# የህግ የበላይነት የሰላማዊና የሰለጠነ ፖለቲካ መሰረት ነው። መለስ ዜናዊ ህግ በሆነበት ሃገር ግን…

የግንቦት 7 ንቅናቄ አካሄድ በየጊዜው በሚነሱ እርባና ላላቸውና ለሌላቸው ጉዳዮች መልስ እየሰጠ መጓዝን አያጠቃልልም። የግንቦት7 ንቅናቄ ምሎና ተገዝቶ፣ ለንቅናቄው አባላትና ደጋፊዎች ቃል ገብቶ፣ ስራ የጀመረው፤ ከእዚህ ቀደም ሌሎች ድርጅቶችና ቡድኖች የገቡበትን አሳፋሪ የፖለቲካ ተዋስኦ (discourse) ባህል ላለመድገም ነው። በበኩላችን ጨዋው የኢትዮጵያ ህዝብ እስካሁን የፖለቲካ ሰዎች ነን ከምንል ግለሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች ካየውና ከታዘበው፣ ቆሽቱን ሲያበግነው ከኖረው ኋለቀር፣ ጨዋነትና ስልጡንነት ከጎደለው የፖለቲካ ባህል፤ የተሻለ የሚገባውና የሚመጥን ህዝብ ነው የሚል እምነት አለን። የግንቦት7 አባላትም ለረባውና ላልረባው መልስ በመስጠት በፖለቲካው ውስጥ ለሚነሳው መካረርና ይህ ለሚቀሰቅሰው ምሬት፣ ምሬቱ ለሚፈጥረው ህሊና መሳት፣ ህሊና ስቶ ለሚከሰተው ብልግና አጋፋሪ የመሆን ፍላጎት የላቸውም። ስድብና አሉባልታ በማሰራጨት ራሳቸውን አዋርደው ሌላውን ወደ ውርደት ጉድጓድ ለመጎተት ለሚፈልጉ አካላት እድል ልንሰጣቸው አይገባም እንላለን። በሌላ በኩል ግን የባለጌን አፍ፣ የውሸታሞችን የአሉባልታ ናዳ፣ ባለጠመንጃንና ባለገንዘብን፣ ቃልቻና ባለውቃቢን፣ ዝነኛንና ባለስምን፣ ጠንቋይንና አስማተኛን፣ ድግምት ደጋሚንና ጥላወጊን ፈርተን፣ በስመ አጉል መቻቻል መደደርደሪያ ላይ ሰቅለን የምንተዋቸው፣ ሃገርንና ወገንን የሚመለከቱ መሰረታዊ ጉዳዮች ከቶውኑ ሊኖሩ አይገባም። ከቶውኑ አይኖሩም እንላለን። ይህ የግንቦት7 የማይናወጥ አቋም ነው።

ግንቦት7 እንዴት እንደተመሰረተ፣ ለምን እንደተመሰረተ፣ ለጉዳዩ ባለቤት ለሆነው ህዝብ ከንቅናቄያችን እለተ-ውልደት አንስቶ፣ በተለያዩ መንገዶች፣ በረጃጅም ጽሁፎች፣ በበራሪ ወረቀቶች፣ በራድዮ በተላለፉ ቃለ መጠይቆች ስናስረዳ ቆይተናል። በሃገር ውስጥና በሃገር ውጭ የሚገኘው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ይህንን የንቅናቄውን አላማ ለመረዳት እንዳልተቸገረ እናውቃለን። የእዚህ ማስረጃው ባለፉት ጥቂት ሳምንታት፣ በመለስ አገዛዝ የሚዘወሩ የመገናኛ አውታሮች፣ ቴሌቪዥንና ሬድዮ ጣቢያዎች፣ ሪፖርተርን የመሰሉ ጋዜጦች፣ አይጋ ፎረምና ተዛመጅ ድረ-ገጾች በጋራ የሚያሰሙት ጩኸት ነው። ግንቦት7 የንቅናቄውን የፖለቲካ አላማ፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ የሁሉም የፖለቲካ ድርጅቶች አላማ ሆኖ ተቀባይነት እንዲያገኝ ያቀረበውን ሃሳብና የሚያደርገውን ጥረት ሲያጣጥሉ ይደመጣሉ። ይነበባሉ። ንቅናቄው አላማው ተቀባይንት እንዲያገኝ በተለማቸው የተለያዩ ዘዴዎችና ይህንን አላማ ለማሳከት በሚከተለው ሁለገብ የትግል ስልት ላይ የሚያኪያሂዱት የተከላካይነት ፕሮፓጋንዳ የሚገርም ደረጃ ላይ ደርሷል።

የወያኔ የሚድያ አውታሮች ግንቦት7ን የጥቃት ኢላማቸው አድርገው መንቀሳቀሳቸው ግንቦት7 ጥሩ ስራ እየሰራ ለመሆኑ ማስረጃ ነው። ሊያሳስበንና ሊያስጨንቀን ይገባ የነበረው፤ የምንለውን ነገር ትክክለኛት ተቀብለው የወያኔ ኢህአዴግ የሚድያ ተቋማት ቢያስተጋቡ ነበር። ወይንም በንቀት ዝምታን ቢመርጡ ነበር። ድርጊታቸው፣ ስለመለስ ዜናዊ ሃገር ሻጭነት፣ ከሃዲነት፣ ዘራፊነት፣ ነፍሰ- ገዳይነት፣ ዘረኛ ከፋፋይነት፣ ለኢትዮጵያችን የከረረ ጥላቻ ያለው ፍጡርነት፣ የምናስተላልፈው መልእክት እያሳሰባቸው መምጣቱን ነው። መለስና የጥፋት ሸሪኮቹ ህሊናና ስብእና ያልዘራባቸው፣ እኩይ ባህርያትን የተላበሱ ፍጥረቶች መሆናቸውንና ከእንደነዚህ አይነቶቹ፣ የረከሰ ጸረ ኢትዮጵያ ነገሮች ጋር የሚደረግ ትግል ሁሉንም አይነት የትግል ስልት (አመጽንም ጨምሮ) የሚደረግ መሆን እንዳለበት ንቅናቄያችን የሚሰጠው መግለጫ የመለስን አፈቀላጤዎች እንቅልፍ እየነሳቸው መሆኑን ነው።

ሰሞኑን የመለስ አምባሳደሮች ሳሙኤል አሰፋና ተስፋዬ ሃቢሶ "እውነተኛ ዴሞክራሲ ግንባታ ረጅም ግዜ የሚፈጅ እንደሆነና ይህ ግንባታ በኢትዮጵያ በመለስ ዜናዊ የተጀመረ መሆኑን፣ የተቃዋሚው ችግር ሁሉን አሁን ውለዱ የሚል፤ ዴሞክራሲ እንዴት ሊገነባ እንደሚችል ለማወቅ ድንቁርናቸው እንቅፋት የሆነባቸው ናቸው::" የሚል መግለጫ መስጠት ተገደዋል። የአገዛዙ ተቋማትም በሃገራችን የዴሞክራሲ ግንባታ፣ "ውሾቹ እየጮሁም በቆራጡ አብዮታዊ ዴሞክራት በመለስ ዜናዊ መሪነት እየተካሄደ እንደሆነ፣ በእዚህ ግንባታ ውስጥ ህግ የሚያከብሩ ተቃዋሚዎች ቦታ እንዳላቸው፣ ነገር ግን በተቃዋሚነት ስም ግንባታውን አሻጥር ለመስራት የሚፈልጉ በሙሉ፣ የስርአቱ ጠንካራ ክንድ እንደሚደቁሳቸው" ማስጠንቀቂያ ሲሰጡ ይደመጣል።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንም "ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ መታገል ለሚፈልጉት፣ ይሄው መንገዱ ክፍት ነው" በማለት አቶ ስዬ አብረሃን ያህል የመለስ ደመኛ፣ መድረክ የተባለውን የድርጅቶች ስብስብ ሲመሰርት ዜና አድርጎ አቅርቧል። ራድዮኑም ይህንኑ ዜና ሲያስተጋባ ነበር። ዋናው የወያኔ ድረ- ገጽ አይጋ ፎረም "ጨለምተኞቹ ግንቦት 7ቶች፣ ተቃዋሚ ድርጅቶች መላወስ የሚችሉበት የፖለቲካ መድረክ የለም" ይላሉ። በሃገር ቤት ግን እነስዬ መድርክ ያቆማሉ የሚል ተረት-ተረት ሲያስነብበን ከርሟል።

ሪፖርተር የተባለው የወያኔ ኢህአዴግ ጋዜጣ ከሁሉም ፈቀቅ ብሎ በመሄድ፣ በአንድ ወቅት የጻፍኩትንና የሃገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታና በተለይ የመለስን አገዛዝ ምንነት የገመገምኩበትን ባለ31 ገጽ ጽሁፍ ለሚያብጠለጥል ድርሰት ሰፊ ቦታ መድቦ የጻፈውን አይቻለሁ። ሪፖርተርም እንደሌሎቹ

የወያኔ ኢህአዴግ የሚድያ ወንድሞቹ ለማለት የፈለገው፣ የመለስ መንግስት ለዴሞክራሲ የቆመ መሆኑን፣ ግንቦት7 እንደሚለው አፋኝ አለመሆኑን፣ ህጋዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ ህገ-መንግስቱንና በህገ- መንግስቱ መሰረት የተቋቋሙ መንግስታዊ ተቋማት፣ እንደ ምርጫ ቦርድ፣ የፍትህና ሌሎችንም ተቋማትን አክብረው ለመንቀሳቀስ ለሚፈልጉ አሁንም ሰፊ እድል እንዳለ ነው፡፡

ከእዚህ በተጨማሪ ብዙዎቻችንን ያስገረመው የዲ.ኤል.ኤ ፓይፐር የፖለቲካ ድለላ ድርጅት ወኪሎች ዶ/ር ብርሃኑ ነጋን ለመሞገት በአውሮፓ ፓርላማ ያቀረቡትን ጥያቄ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ለመታገል የሚቻልበት መድረክ እንዳለ ለመግለጽ ብቻ፣ ከአሜሪካ ተነስተው አውሮፓ ድረስ ተጉዘው አይተናል፡፡ የዲ ኤል. ፓይፐር ደላሎችም ሆኑ አይጋ ፎረም ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ እንደሚቻል ብቻ ሳይሆን የመቻሉ ማስረጃ አድርገው የሚያቅርቧዋቸው ምሳሌዎች፣ የወያኔ ባለስልጣናት ገና አገር ገዢዎች ከመሆናቸው በፊት፣ ከእዛም በኋላና አሁንም ቢሆን ተወዳደሪ በማይገኝለት ከፍተኛ ጥላቻና ምሬት የሚያዩዋቸውን ግለሰቦች ( ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም) መሆኑ ደግሞ በሃፍረተ-ቢስነታቸው እንድንገረም የሚያደርገን ነው፡፡

ለግንቦት7 ይህ የወያኔ ኢህአዴግ መጨበጫ መያዣ የሌለው አስገራሚ ፕሮፓጋንዳ የሚያሳየው ንቅናቄው እየሄደበት ያለው አቅጣጫ እንደተለመደው "መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ" በሚል ንቀት በመለስና በተላላኪዎቹ መታለፍ የማይቻል አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን ነው፡፡ ህግ መለስ ዜናዊ በሆነበት ሃገር፣ የመለስን ህግ በመጣስ፣ ማንኛውንም የትግል ስልት አመጽንም ጨምሮ ህዝብ መብቱን ነጻነቱን፣ አንድነቱንና የሃገሩን ዳር ድንበር ለማስከበር ለመስዋእትነት ቆርጦ በመነሳት መታገል እንዳለበት በህዝብ ውስጥ ቅስቀሳ ማድረግ፣ ህዝብን ማደራጀት መዘዙ ብዙ እንደሆነ ወያኔ ኢህአዴግ ማየት ችሏል ማለት ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ ወቅት ግንቦት7 የፖለቲካ አላማውንና ይህን አላማ ለማሳካት የሚከተለውን የትግል ስልት ለህዝብ የበለጠ በማስተዋወቅ፣ ያዋጣል ብሎ ላሰበው እምነቱ የህዝብን ደጋፍ ያሰባስባል እንጂ ምክንያት ላይ ያልተመሰረተን ዝምታ አይፈቅድም፡፡ ዛሬ በእዚህ ቦታ የምናደርገው ስብሰባ፣ የሚቀጥለውም ረቡእ በላስቬጋስ ከወገኖቻችን ጋር የምናደርገው ምክክርና ውይይት አላማው በመለስና በጋሻ ጃግሬዎቹ ቤት በመታየት ላይ ያለውን ግራ መጋባትና መተራመስ ለማባባስ የሚያስችል ሁለገብ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሲባል ነው፡፡  ይህንን ድጋፍ ለማሰባሰብ ደግሞ አላማችንን በዝርዝር የሚያብራራ ጽሁፍ መጻፍ፣ ቃለ-መጠይቅ መስጠት፣ አላማችንን በቃል ማብራራት ይጠይቃል፡፡

ከእዚህ ቀጥሎ የተለያዩ እርእሶችን በመጠቀም ይህንኑ የማብራራት ስራ ለመስራት እንሞክራለን።

1. ግንቦት7ን ምን አመጣው?

ከእዚህ ቀደም ደጋግመን በቃልም፣ በጽሁፍም ለማስረዳት እንደሞከርነው የግንቦት7 መመስረት በቅንጅት ውስጥ በተለይ በአመራሩ ውስጥ ከተነሳው ውዝግብ ወይም ቀውስ ጋር የሚያገናኘው ጉዳይ የለም። ዛሬ የግንቦት7ን አላማ ደግፈን የምንቀሳቀስ ሰዎች በጋራ እንድንሰባሰብ ያደረገን መሰረታዊ ጉዳይ አንድ ብቻ ነው። ይህ ጉዳይ ዛሬ በስልጣን ላይ ስላለው የመለስ አገዛዝ ምንነት ላይ የደረስንበት የጋራ ግንዛቤ ነው። ይህ ግንዛቤ አንዳንዶቻችን ከምርጫ 97 በፊትም ይዘነው የነበረ ሲሆን ሌሎቻችን ደግሞ ምርጫ 97 አይን ባወጣ መንገድ በመጭበርበሩና ከእዛ በኋላ የመለስ አገዛዝ የወሰዳቸውን የተለያዩ የግፍ እርምጃዎች በመመርመር የደረስንበት ግንዛቤ ነው።

በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ምን አይነት አገዛዝ ነው? ይህ አገዛዝ በተለይ ከምርጫ 97 በኋላ በሃገሪቱ ውስጥ ያሰፈነው ምን አይንት ሁኔታ ነው? ይህ ሁኔታ የሃገራችንን መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያግዝ ነው ወይንስ ቀውሱን የሚያባብስ? የሚሉ ጥያቄዎች ግንቦት7 አንስቷል። ዘርዘር አድርገን ስናየው፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ያለው ሁኔታ፤

- ህዝብ የስልጣን ባለቤት የሚሆንበትን
- የህዝብ መሰረታዊ መብቶች የሚንከባከቡ ተቋማት የሚመሰረቱበትን፣
- ህዝብ መሰረታዊ የፖለቲካና የሲቪል መብቶቹ ተከብረው ከተገዥንት ወደ ዜግነት የሚሸጋገርበትን፣
- ህዝብ ሰላምና መረጋገት አግኝቶ፣ ነጻነትና የጋራ መተሳሰብ ባለበት ሁኔታ ድህነትን፣ በሽታን፣ መሃይምነትን፣ የተፈጥሮና የአካባቢ መራቆትንና ሌሎችንም አደጋዎችና ቀውሶች የሚያስቆምበትን፣
- ህዝብ የሃገሩን ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት እንዳሻቸው የሚሸቅጡ ሃይሎችን ማስቆም የሚችልበትን፣
- በአጠቃላይ ህዝብ ቀደምቶቹ፣ ደማቸውን በየሜዳው፣ በዱርና በሸንተረሩ፣ በየተራራውና በየሸለቆው፣ በየቦረቦሩና በየፈረፈሩ አፍሰውና አጥንታቸውን ከስክሰው፣ አለምን ጉድ ያሰኘ ከፍተኛ መስዋእትንት ከፍለው ባቆዩለት ሃገር ላይ፣ ሊያስኮራ በሚችለው ታሪኩ ኮርቶ እንዳይኖር፣ ሰርቶ እንዳይበለጽግ፣ ወልዶ እንዳይድር፣ አርጅቶ እንዳይጦር፣ ከቀየው እየተነቀለ፣ ቆሌውን፣ አድባሩን፣ ባህሉን ታሪኩን እምነቱን ቋንቋውን ባጠቃላይ የማንነቱ

መሰረት፣ የዝንተ አለም የህልውናው መልህቅ፣ ከሰውም ሰው አድርጋ ያኖረችውን ሃገሩን እየጣለ፣ የብርታቱ ምንጭ ሆና ለእልፍ አመታት ካኖረቸው፣ በገዛ ሀገሩ ላይ ተስፋ እንዲቆርጥ እየተደረገ፣ የባእድ ሃገርን የስደት ህይወት ትልቅ ድል አድርጎ የሚያይበትን አዋራጅ ሁኔታ መቀየር የምንችለበትን እድል እያሰፋ ነው ወይንስ እያጠበበ፣ የሚል ጥያቄ ግንቦት 7 በቅድሚያ ካነሳቸው ጥያቄዎች መሃል ጥቂቶቹ ናቸው።

መልሳችን ዛሬ በሃገራችን ያለው ሁኔታ በችግር ላይ ችግርን በቀውስ ላይ ቀውሰን የሚደርብ እንጂ ከቀውስ የምንወጣበትን ሁኔታ የሚግዝ አይደለም የሚል የማያሻማ መልስ ሆኗል።

ይህንን እየተባባሰ ያለን ሁኔታ በፍጥነት መቀየር ካልቻልን፣ ሁላችንም የእዛች ሃገር ሰዎች፣ አስከዛሬ ከገጠሙን ችግሮችና ፈተናዎች ይበልጥ ለከረሩና መውጫ ወደማይኖራቸው ቀውሶች ውስጥ እንወድቃለን የሚል ከፍተኛ ስጋት ግንቦት7 አለው።

ይህንን ስጋት በዘገምተኛ ሂደት ማሰቆም አይቻልም። ኢትዮጵያ እድልና ጊዜ እንደልቧ ያላት ሃገር አይደለችም። መለስ ዜናዊ ህሊና ገዝቶ፣ ይች ሃገር ምንም እንዳልበደለቸው፣ የበደሉት እንደ ጅግናው የትግራይ ወገናቸው በአርበኛነት ጣልያንን ማርበድበድ ሳይሆን ለጣሊያን በባንዳነት በማደር አሳፋሪ ቅርስ የተውለት፣ ይህ ውርደት ከጫነባቸው ማህበራዊ የውርደት ሙጫ መላቀቅ ሳይችሉ ቀርተው፣ የጸረ- ኢትዮጵያ ሰሜት ተክለውበት ያለፉት ቀደምቶቹ እንደሆኑ ተረድቶ፣ ኢትዮጵያን በጎዋን ሊመኝላት እስከሚችል ድረስ በትእግስት እንጠብቀው በሚል ቀቢጸ- ተስፋ፣ ችግሯ በይደር የሚቀመጥ ሃገር አይደለችም። ዛሬ! በበደል ፊት፣ በአፈና ፊት፣ በሃገር መሸጥ ፊት፣ በዘረኛነት ፊት፣ በዘራፊነት ፊት ትእግስታችን ሊሟጠጥ፣ የሃገራችንንና የሁላችንም በጎ እንደማይመኙ የተትረፈረፈ መረጃ በእጃችን ያስረከቡን ግለሰቦች በቃችሁ ልንላቸው፣ በእልህና በቁጭት ልንነሳ የሚገባን ወቅት ነው ብለን እናምናለን። የገባንበትን አስፈሪ ቀውስ ለመወጣት አምርሮ ከመታግል ሌላ አማራጭ የለንም ብለናል።

ትግላችን ለምን ይሆናል ለሚለው ጥያቄ ግንቦት 7 መልስ ሰጥቷል። ከላይ የጠቀስነው አሳፈሪና አዋራጅ ወቅታዊ ሁኔታ በተሻለ፣ ለሁሉም የሃገሪቱ ዜጎች በሚጠቅም ሁኔታ መቀየር ነው። ይህም ምን ማለት እንደሆነ በንቅናቄው ፕሮግራም ላይ ዘርዝረን አስቀምጠናል። በፕሮግራማችን ላይ ያስቀመጥናቸው መፍትሄዎች፣ ብዙዎች በቀላሉ የሚስማሙባቸው እናንተም ከድረ ገጻችን ላይ ማንበብ የምትችሉት ነው።

በእዚህ ላይ ግዜ ለላመጥፋት ወስኛለሁ።

ቀጥዬ የምተላለፈው ግንቦት7 የሃገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ከገመገመ በኋላ ንቅናቄው ወደ አነሳውና በጣም ወሳኝና አነጋገሪ ጉዳይ ነው። መታገል ምርጫ ሳይሆን ግዴታ ከሆነ፣ ጥያቄው እንዴት እንታገል የሚለው ነው።

## 2. የእንዴት እንታገል ጥያቄና ግንቦት7

ግንቦት7 እንዴት እንታገል የሚለውን ጥያቄ ሲያነሳ 4 አማራጮችን አይቶ ነበር።

ሀ) ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ

ለ) ሰላማዊም ህጋዊም ባልሆነ መንገድ

ሐ) ሰለማዊ ሆኖ ግን ህጋዊ ባልሆነ መንገድ

መ) ህጋዊ ባልሆነ ነገር ግን የሰላማዊና የአመጽ ስልትና አማራጮችን በሙሉ በሚጠቀም መንገድ

እነዚህን አራት አማረጮች በቂ ጊዜ ሰጥተን በጥሞና ተራ በተራ ተመልክተናቸዋል።

**የጀመሪያውን ህጋዊና ሰላማዊ አማራጭ ወስደን ስንመለከት፤**

- ይህ አማራጭ በብዙ መልኩ ከአራቱ አማራጮች የተሻለው ይሆን እንደ ነበር፤ ሰላማዊ የሚለው ላይ ምንም ችግር ባይኖርበትም፣ ህጋዊ የሚለው ግን ትልቅ ችግር የሞላው መሆኑን፤
- መለስ ዜናዊ ራሱ ህግ በሆነበት ሃገር ተራ የሲቪል መብቶች፣ የተቃውሞ ሰልፍ ማድረግ ፣መሰብሰብና ሃሰብን በነጻነት መግለጽ የሚያስከስስ፣ የሚያሳስርና የሚያስገድል መሆኑን፤
- ለዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣ ለብዙ ችግሮቻችን መፍቻ ቁልፍ ናቸው ብለን የምናስባቸውን፣ ህዝብን የስልጣን ባለቤት በማድረግ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱትን፣ ስለምርጫ ከማውራት በፊት፣ ሰለፓርቲዎች ፉክክርና ስለፓርቲዎች የተለያዩ ፖሊሲዎች ልዩነት ከመነጋገር በፊት፣ በቅድሚያ መመስረት አለባቸው የምንላቸውን ነጻ መንግስታዊ ተቋማት ጥያቄ ማንሳት በሃገር ከህደት፣ ህግ-መንግስቱን በመጣስና በዘር ማጥፋት ወንጀል በሚያስከስስበት፣ እንዲህ አይነቱ አሳፋሪ የህግ ቧልት በሰፈነበት ሃገር፤
- በተለይ ዛሬ ከእኔና ከሌሎች ባልደረቦቼ ጋር በግንቦት 7 አመራር ውስጥ ያሉ ከእስር የተፈቱ ወንድሞቼ፣ እነዚህን ተቋማት ይፈጠሩ የሚል ጥያቄ ላለማንሳት፣ በአንድ አጋጣሚ ብርታቱን አግኝተው ቢያነሱ በይቅርታ የተነሳላቸው የእድሜ ልክ እስራት ተፈጻሚ እንደሚሆን ፈርመው ከእስር እንዲወጡ፣ ፍትህን በጭንቅላቱ ባቆመ ኢፍትሃዊ የህግ ስርአት በነገሰበት ሃገር፣ ህጋዊ በሆነ መንገድ መንቀሳቀስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ግንቦት7 በጥሞና

መርምሯል። በእኛ አመለካከት በእንዲህ አይነቱ ፍትህና ህግ የሚባሉ፣ አንድን ማህበረ-ሰብ እንደ ማህበረሰብ አድርገው ለማስቀጠል፣ ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ የፍትህና የህግ እሴቶች ማላገጫ በሆኑባት ሃገር፣ በህጋዊ መልኩ የሚደረግ ትግል፣ ለሁሉም በእኩልነት የሚሰራ ህግ ሳይሆን የመለስ ዜናዊ አምባገነናዊ ፍላጎት በሚዘውረው ቀጭን ትእዛዝ መሰረት መንቀሳቀስን የግድ የሚያደርግ ይሆናል የሚል ስጋት አለን። በእኛ እምነት የሰላማዊና የህጋዊ ትግል አማራጩ ይህ ከሆነ፣ እንዴትም ከእዚህ ውጭ ሊሆን እንደሚችል ለመረዳት ከተቸገርን፣ ቀደም ብዬ ያቀረብኳቸውን በሃገራችን ውስጥ እየተባባሱ በመሄድ ላይ ናቸው ያልኳቸው ችግሮች፣ የበለጠ ሲባባሱ እያየን እጃችንን አጣጥፍን ከማየት ውጭ አማራጭ ላይኖረን ነው ማለት ነው። ይህንን አማራጭ አድርጎ መውሰድ ሺህ ጊዜ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ፣ የሰላማዊና የህጋዊ ትግሉ ተመራጭ ነው ብለን ብናምንም አማራጭ አድርግን ልንወስደው አልተቻለንም።

- በግንቦት7 በኩል የመለስ ዜናዊን ጸረ ህዝብና ጸረ ሃገር አገዛዝ አጠቃላይ ባህርይ፣ አውጥትን አውርደን በቅጡ ከመረመርን በኋላ፣ ይህ አገዛዝና በእዚህ አገዛዝ ስር የተፈጠረው እጅግ አፋኝ የሆነ ሁኔታ፣ ህጋዊ የሆነ ሰላማዊ ትግል በሃገራችን ማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ መስፈኑን አስገንዝቦናል። በተለያዩ የአለማችን  ክፍሎች እንዳየናቸው በሰላማዊ እንቅስቃሴ ለውጥ ማምጣት የተቻሉባቸው ሁኔታዎች ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ በሃገራችን አለመኖሩን፣ እንዳውም የሃገራችን ሁኔታ ሰላማዊ ትግል ተሞክሮ ያልሰራባቸውን ወይም በጠቅላላ የከሸፈባቸውን ወይም መስራቱ ከተስፋ በላይ ትርጉም የማይታይባቸውን፣ የበርማንና የቲቤትን ሁኔታ ወይም ህዝብ ከአቅሙ በላይ በሆነ አፈና አንገቱን ደፍቶ ያለቀባቸውን ፋሽታዊ አገዛዞች እንጂ፣ የህግ የበላይንት የነበረባቸውን የጋንዲዋን ህንድ አሊያም የማርቲን ሉተርንን የ1950ዎቹና 60ዎቹ አሜሪካ ጋር ፈጽሞ የማይመሳሰል  መሆኑን ለማየት በቅተናል። በእዚህ ግምገማችን በጣም ግልጽ ሆኖ የወጣ ጉዳይ በአደባባይ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ለለውጥና ለመብት የሚደረግ ትግል በተወሰነ ደረጃ ለህግ ክቡርነት፣ ለፍትህ ታላቅነት የተወሰነ ቦታ የሚሰጡ ገዥዎች ወይም ስርአቶች ባሉበት ቦታ ብቻ የሚደረግና የሚቻል እንደሆነ ነው። ህገ-መንግስት ውስጥ የሰፈሩት ህጎች ከተጻፉበት ወረቀትና ቀለም ውጭ ህልውና ትርጉም አጥተው፣ ህግ በመለስ ዜናዊና በአፋኝ ጓደኞቹ ፍላጎት በተተካበት ሃገር፣ ህጋዊ የሆነ ሰላማዊ ትግል ሊታሰብ አይችልም ባዮች ነን። ይህ ደግሞ ትልቅ መሰረታዊ የሆነ የፖለቲካ እምነት ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ተረድቶ ከችግር

መውጫውንና ሃገሩን ማዳን የሚችልበትን አማራጭ እንዲፈልግ መቀስቀስ ተገቢም ነው ትክክልም ነው ብለን እናምናለን።

እግረ መንገዴን ለማሳሰብ የምፈልገው ይህ ትንተና የመለስ አገዛዝን ኢላማ ያደረገ እንጂ ህጋዊና ሰላማዊ ትግል ይቻላል ያሉትን ድርጅቶችንና ግለሰቦችን ኢላማ ያደረገ አይደለም። እኛ አይቻልም ብለን በወሰነው ሃገራዊ ሁኔታ ውስጥ ይቻላል ብለው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ባመኑት መንገድ መንቀሳቀስ መብታቸው እንደሆነ እናውቃለን። ከእዛም አልፈን ህጋዊ የሆነው ሰላማዊ ትግላቸው እንዲሳካለቸው እንመኛለን። እነዚህ ግለሰቦችና ድርጅቶች በግላቸው ትክክል ነው የሚሉትን የትግል ስልት ሲመርጡ እንደኛው ተጠበውና ተጨንቀው ነው ብለን እናስባለን። ምርጫቸው፣ እንደኛው ለሃገርና ለወገን በጎ ከማሰብ ኪሚመጣ ቅን ፍለጎት የመነጨ ነው ብለን እናምናለን። እድል አግኝተው ቢሰካላቸው፣ እኛ እድል አግኝተን ቢሰካልን ለህዝብ ቃል የገባነውን ለመፈጸም አለን ብለን የምናስበውን ታማኝነት እነሱም አላቸው ብለን እናምናለን። የእኛ ችግር በሃገር ውስጥ ያለው ህግንና ፍትህ ማእከል ያላደረገ፣ በህገ-አራዊት የሚመራ አገዛዝ የእነዚህን ወገኖቻችን ስልጡንነት፣ ቀናነትና አርቆ አሳቢነት እድል ሰጥቶ ማስተናገድ ቀርቶ፣ እንዲህ አይነት አስተሳሰብ በሰዎች አእምሮ ሊበቅል ይችላል ብሎ መገመት የማይችል ነው፤ የሚል ነው። በተለይ እኔ ይህን የምናገረው ዛሬ በስልጣን ላይ ያሉትን ገዥዎች ስነ ህሊናና አስተሳሰብ በቅርበት ለማጥናት በአንድ ወቅት እድል በማግኘቴ ነው።

በተለያዩ አጋጣሚዎች ግንቦት7 የሚሰጠው አስተያየት፣ ሁሉንም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ የሃገሪቱን ዜጎች ሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ እንታገላለን የሚሉትንም የማይሉትንም፣ እኛንም፣ ባጠቃላይ ሁላችንንም አፍኖና ቀጥቅጦ በሚገዛው የመለስ አገዛዝ ላይ ያነጣጠረ እንጂ ሰላማዊና ህጋዊ ትግል እናደርጋለን በሚሉ ላይ ያነጣጠጠረ አይደለም።

በሃገራችን ስላለው ነባራዊ ሁኔታ ያለን ትንተና ግን ከእነዚህ ሃይሎች ትንተና ጋር የማይጋጠም በመሆኑ ብቻ በመጥፎ አይን እንዲያዩን አንፈልግም። በእኛ በኩል ሰላማዊና ህጋዊ ትግል ይቻላል የሚል፣ ከኛ የተለየ ትንተና ሰዎች ስላላቸው በመጥፎ አይን እንደማናያቸው ሁሉም እንዲያውቅልን እንፈልጋለን። ከእዚህ በላይ የገለጽኩት በዋንኛነት ለምን ህጋዊ በሆነ መንገድ የሚደረግን ትግል እንዳልመረጥን ለምንስ ከቀድሞ ድርጅታችን ከቅንጅት ለቀን ሌላ ንቅናቄ ለማቆም እንደተገደድን በሚገባ ይገልጻል ብዩ አምናለሁ።

**በሁለተኛው ደረጃ የተመለከትነው አማራጭ ሰላማዊም ህጋዊም ባልሆነ መንገድ መታገል የሚለውን አማራጭ ነው፡፡**

ይህ አማራጭ ለሰላማዊ ትግል ምንም ቦታ የማይሰጥ፣ ጠቅላላ ትግሉን በአመጽ ላይ ብቻ እንዲያተኩር የሚያደርግ አማራጭ ነው፡፡ ንጹህ የትጥቅ ትግል አማራጭ ማለት ነው፡፡ በእኛ እምነት በሃገሪቱ ውስጥ ያለው የህዝብ ምሬት በታሪካችን ታይቶ ከሚታየው ደረጃ በላይ አልፏል፡፡ ህዝብ በደልና ግፍ የሚሸከምበት አቅሙ ተሟጦ አልቋል፡፡ በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ በሰራቸው አስነዋሪና አሳፋሪ ስራዎች በህዝብ የተተፋ ሆኗል፡፡ ይህ ሁኔታ ሰፊ የሆነ የህዝባዊ እምቢተኛነት የሰላማዊ እንቅስቃሴ በህቡእ ማደራጀት የሚያስችል ነው የሚል እምነት አለን፡፡ በሌላ በኩልም ከምርጫ 97 ጋር ተያያዞ ህጋዊ በሆነ መንገድ፣ በከፍተኛ መስዋእትነትም ቢሆን ህዝብ የተማራቸው፣ በሰለማዊ መንገድ የመታገል ልምዶችና እውቀት አለው፡፡ ይህንን እውቀቱንና ልምዱን እንዳለፈው ጊዜ ራሱን ለጥቃት ሳያጋልጥ፣ ህግና ህገ መንግስት አለ ብሎ ሳይዘናጋ በጥንቃቄና በሚስጥር በመደራጀት በስራ ላይ ማዋል ይቻላል ብለን እናምናለን፡፡ እንዲህ አይነቱንም አደረጃጀት ለመፍጠር አቅማና ብቃቱ አለን እንላለን፡፡ በመሆኑም የመከራ እድሜያችንን ለማሳጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚኖረውን ሰላማዊ የትግል ስልት ግምት ውስጥ ያላስገባ፣ በአመጽ ላይ ብቻ የቆመን የትግል ስልት ልንቀበለው ፈቃደኞች አልሆንንም፡፡

**በሶስተኛ ደረጃ የታየው አማራጭ ለአመጽ ቦታ የማይሰጥ ነገር ግን በህቡእ የሚደራጅ የሰላማዊ ትግል አማራጭ ነው፡፡**

በህቡእ የሚደራጅ ሰላማዊ ትግል፣ ህዝብ በህገ-መንግስቱ የተቀመጡትን ህጋዊ መብቶቹን ለማስከበር የሚያደርገው ፍትሃዊ ትግል ቢሆንም፣ እነዚህን መብቶች በአደባባይም ሆነ በድብቅ ተደራጅቶ ለማስከበር መሞከር፣ በመለስ አገዛዝ ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ለጥቃት መጋለጡ አይቀርም፡፡ የጥቃቱ አይነት ደግሞ ምን ያህል አረመኔያዊና ጨካኝነት የተሞላው እንደሆነ አይተናል፡፡ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ በድብቅና በህቡእ የሚደራጀው ሰላማዊ ትግል ራሱን ለመከላከል የሚችልበትን አቅም ማዳበር ይኖርበታል፡፡ ይህ የመከላከል አቅም ለሰላማዊ ትግል አድራጊው ህዝብ የልብ ልብ እንዲሰማው የሚያደርግ፣ ሊያፍኑት የሚፈልጉትም እንደለመዱት በማን አለብኝነት እየተነሱ ያለምንም ፍራቻና የአጸፋ ጥቃት ህጻናትና እናቶች እየጨፈጨፉ መኖር የሚችሉበት ሁኔታ አለመኖሩን በማሳየት፣ ከእበሪታቸው ትንሽም ቢሆን እንዲታቀቡ ማድረግ የሚችል መሆን አለበት

ብለን እናምናለን። ስለሆነም እራሱን ከጥቃት መከላከል የማይችል በድብቅ የተደራጀ የሰላማዊ ትግል ዘዴዎችን ብቻ በስራ ላይ የሚያውል ንቅናቄ አንሆንም ብለናል።

ከእዚህ ጋር ተያይዞ የተመለከትነው ሌላው ጉዳይ፣ በሃገሪቱ ውስጥ በዘውግ አደረጃጀት ይሁን በዘውገ-ብዙነት ተደራጅተው የአመጽ ትግል ከሚያደርጉ ድርጅቶች ጋር በህብረት መስራትና እነዚህን የአመጽ እንቅስቃሴዎች የአጠቃላዩ የሃገራችን የፖለቲካ ቀውስ አጠቃላይ የመፍትሄ አካላት እንዲሆኑ ካለን ፍላጎት በመነሳት፣

አንደኛ፣ በመርህ ደረጃ አመጽን ያገለለ አካሄድ ብቻ የሚል አቋም በግንኙነታችንን ላይ ሊፈጥረው ስለሚችል ችግር፣

ሁለተኛ፣ ግንቦት7 ያስቀመጠውን የፖለቲካ ፕሮግራም ለማስፈጸም፣ ከሌሎችም ሃይሎች ጋር በሚፈጥረው ህብረት ውስጥ የሚደረሰበት ስምምነት በጉልበተኞች የሚቀማበትን፣ ከሃይል መበላለጥ የሚመጣ እድል ከፍት አድርጎ ላለመሄድ በማሰብ፣

ሶስተኛ፣ ግንቦት7 የተሸከመውን የፖለቲካ እምነትና ይህንን እምነት ደግፎ ይቆማል ብልን የምናስበውን በርካታ ኢትዮጵያዊ ፍለጎት ለመከላከል፣ የመደራደሪያ አቅም ፈጥሮ መገኘት አስፈላጊ ነው የሚል እምነት አለን። በህቡእ የተደራጀ ሰላማዊ ትግል ብቻ እንዳንል ካስገደዱን ምክንያቶች ውስጥ እነዚህንም መጨመር ትችላላችሁ።

በስፍንና ይሆን በመላምት፣ ለሌሎች በጎነትና ቀናናት ላይ ብቻ መተው የሌለባቸው ሃገረዊና ህዝባዊ ጉዳዮች እንዳሉ ከላፈው ታሪካችን ተምረናልና ድርጅታዊም ሆነ ተቋማዊ ጥበቃ በሌለው መንገድ ከእዚህ በኋላ ላለመጓዝ ወስነናል።

**በአራተኛ ደረጃ የተመለከትነው አማራጭ በመለስ ዜናዊ አይን ህጋዊ በማይባል በህገ-መንግስቱ ግን ህጋዊ ሊሆን ይችል የነበረን የመብት ጥያቄ ለማንሳት በሚስጥር ተደራጅቶ፣ ሁሉንም አይነት የሰላማዊና የአመጽ አማራጮችን እንደ አስፈላጊነታቸው በስራ ላይ ለማዋል የምንችልበትን ነጻነት የሚያላብሰን አማራጭ ነው።**

ይህ አማራጭ የሰላማዊ ትግሉ መጠናከርና መደፋፈር፣ በሚፈጠረው የለውጥ ሁኔታ ከሚመጡ አዳዲስ ጉልበተኞች ንቅናቄያችንንና ህዝብን ለመከለከል የሚያስችል እድል ከመስጠቱም በላይ ሌላ ጠቀሜታ እንዳለው አይተናል። ይህ አማራጭ ለመለስ ዜናዊ አገዛዝ አስቀድመን ምን እንደምናደርግና እንደማናደርግ መረጃ በመስጠት፣ ይህን ያደርጋሉ ያንን አያደርጉም የሚል እፎይታ የማይሰጥ ነው። እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜውን፣ ቦታውንና ስልቱን የምንመርጠው፣ በስራ ላይ የምናውለው እኛ እንጂ ወያኔ ኢህአዴግ አይሆንም። እንዲሆንም የማይፈቅድ ነው። ይህ ደግሞ አገዛዙ ከየት ቦታ ምን ሊመጣበት እንደሚችል በማያውቅበት፣ ተዝናንቶ መኖር ወደ ማይችለበት ሁኔታ የሚጨምረው፣ ሞራሉን የሚያላሽቅ ከብዙ አቅጣጫዎች ግራ የሚያገባውን ስራ የመስራት ነጻነት የሚሰጠን ይሆናል። ይህንን ብዙዎች ‹ሁለገብ የትግል ስልት› እያሉ የሚጠሩትን አማራጭ የመረጥነው ከእዚህ በላይ ባቀረብናቸው ምክንያቶች ነው።

**ለማጠቃለል**

ግንቦት7 የፖለቲካ ፕሮግራሙን ለመቅረጽ፣ የትግል ስልቱ ምን ይሁን ብሎ ለመወሰን፣ ከተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ምን መሰረታዊ መርሆዎች ያካትት የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በርካታ ሰነዶችን አዘጋጅቶ በበርካታ ጉዳዮች ላይ ወይይት አድርጓል። ለምሳሌ ያህል፤

- የአለም የፖለቲካ ሁኔታ መቀየር፣ ከአመጽ ጋር የተያዘ እንቅስቃሴ መፍጠርና ይህ ሁኔታ የሚኖረው ተጽእኖ፣ በኢትዮጵያ ዙሪያ የሚገኙ መንግስታትና ባህሪያቸው፣
- መለስ ዜናዊ እንዳሻው የሚያዘው የጦር የስለላ የፖሊስ ሃይል የገንዘብ ጉልበት፣ ለአሽክርናው የሚከፍሉት ሃያላን መንገስታት ያሉት መሆኑን ይህ እውነታ ትግሉን በማክበድና በማወሳሰብ ደረጃ ያለውን ጫና መርምረናል።
- የአመጽን ትግል በመኮነን የሰላምን ትግል በማጉላት በህበረተሰቡ ውስጥ የፈጠርነው ስሜት አሁን መደረግ አለበት የምንለው ሁለ-ገብ የትግል ስልት ተቀባይነት እንዲኖረው በምናደርገው ጥረት የሚኖረውን ጫና ፣
- አመጽ የታከለበት ትግል የምንመኘውን ዴሞክራሲያዊ ስርአት በመገንባትና ህዝብ የስልጣን ባለቤት ለማድረግ ባለን ፍላጎት ላይ ሊፈጥር ስለሚችላቸው ደንቃራዎች፣
- በአመጽ ትግሉ በዋንኛነት መስዋእትነት የሚከፍለው የህብረተሰብ ክፍል የቱ ይሆናል፣ የአመጽ ትግሉ ለሚፈጥረው የሰው ህይወትና የንብረት መጥፋት ምን አይነት የሞራል ቅቡልነት (moral legitimacy) ሊኖረው ይቻላል?

- አንድ የፖለቲካ ድርጅት ትልቅ ጉልበት ለብቻው በማዳበርና ለብቻው ስልጣን ይዞ እንደገና ሌላ ዙር አምባገነናዊ ስርአት በሁላችንም ላይ ለጭን የሚችልበት አደጋ አለ ወይ ይህንን አደጋ ለመከላከል ምን ማድረግ እንችላለን?
- ከእዚህ በፊት በሃገራችን ተፈጥረው የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ህብረቶች ለምን ፈረሱ? ከአሁን በኂላ የሚፈጠሩት እንዳይፈርሱ ካለፈው ወድቀት ምን ተምረን ምን መጠበቂያ እናበጃለን?
- የፖለቲካ እምነታቸው ምን እንደሆነ፤ በመለስ ዜናዊ አገዛዝ በደንብ የሚታወቁ ግለሰቦች በሃገር ውስጥ ቢቆዩ፣ በህቡእ ለምናደራጀው ሰላማዊና አመጽን ቀላቅሎ ለምናደርገው ትግል ምን አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል? በራሳቸውም ላይ ሆነ በትግሉ ላይ ጉዳት አያስከትሉም ወይ?
- የሃገር ቤቱን እንቅስቃሴ የሚመሩት ግለሰቦችና ምን አይነት መሆን አለባቸው? የሚያዋቅሩት ድርጅት ምን መሆን አለበት? እነዚህንና ሌሎችን ማለቂያ የሌላቸውን የትግሉ ተለዋጮች (variables) በስፋት አንስተን ለረጅም ግዜ አውጥተን አውርደን ያቆምነው እንቅስቃሴ ነው፤ ግንቦት7።

ግንቦት7ን ተቀላቀሉ ደግፉ ስንል፣ ንቅናቄው ብዙ ነገሮች አገላብጦ ያየ፣ እፈጽመዋለሁ በማለት የሚገባውን ቃል ኪዳን መጠበቅ የሚችል ነው ብለን ስለምናም ነው። የእዚህ ንቅናቄ አባል ለመሆን የሚፈለግ፣ በድረ-ገጻችን ላይ በሚገኘው የድርጅት ጉዳይ የኢሜል አድራሻ org@ginbot7.org ጥያቄ ማቅረብ ይችላል። ባጠቃላይ የሃገራችን ህዝብ ለመብቱና ለነጻነቱ መከበር ከሚያደርገው ትግልና ከሚከፍለው መስዋእትነት ጋር ሲወዳደር የድርጅታችንን ድረ-ገጽ ጎብኝቶ የአባልነት ጥያቄ በማቅረብ በሚቻለው ሀሉ ለፍትህ፣ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ የምናደርገውን ትግል መቀላቀል የሚከብደው ይኖራል ብለን አናስብም። የሚቀላቀሉን ግለሰቦች ራሳቸው ፈልገው በአደባባይ መውጣት እስካልፈለጉ ድረስ ማንነታቸው በምንም መንገድ መታወቅ በማይችልበት መንገድ ድጋፋቸውን መስጠት ይችላሉ። የሚቀረው የእናንተ ፍላጎትና ውሳኔ ብቻ ነው።

የግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ
በይቻላል ስሜት በአንድነት ተነስተን የጋራ መከራችንን በጋራ ጥረት እናሳጥር !

ሎስ አንጀለስ ሃምሌ 2000 አ.ም
አንዳርጋቸው ጽጌ